የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ)
Ethiopian People's Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)

## የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ትንሳኤን ለማቅረብ ከፍተኛ የዜግነት ድርሻና ኃላፊነት ካላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የወጣቱ ተሳትፎ የአንበሳውን ድርሻ የሚይዝ ነው።

በባዕዳን ርዳታና ትብብር በትረ ሥልጣኑን ይዞ ላለፉት 18 ዓመታት የሕዝቡን መብት በማፈን፤ የሀገሪቱን ንብረቱን በመዝረፍ፤ ሕዝቡን ለስቃይና ለመከራ የዳረገውንና በኢትዮጵያ ታሪክ፤ ባህልና ቅርስ ላይ ዘመቻ በመክፈት፤ የዘርና የሃማኖት ክፍፍልን በማስፋት የሀገሪቱን ህልውና አደጋ ላይ የጣለውን የወያኔን ሥርዓት አስወግዶ የሕዝቦቿን መብት ያረጋገጠች፤ እኩልነትና አንድነትን ያስከበረች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ በሀገር ቤትና በውጭ ራሳቸውን ሲያደራጁ የቆዩ ወጣቶች በተወካዮች አማካይነት በቺካጎ ከተማ ጉባዔ አካሂደው ዛሬ ሰኔ 22 ቀን 2001 ዓ.ም. (June 29, 2009) የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት(ኢሕአፓ ወክንድ) በሚል ስያሜ የሚጠራ ድርጅት መሥርተዋል።

ጉባዔው በኢትዮጵያ ወቅታዊ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ተነጋግሮ የጋራ ግንዛቤ ይዟል። በኢሕአፓ ወክንድ ዓላማና ተግባር፤ በሕገ ማህበርና በመዋቅር ጉዳዮች ላይ በሰፊው ተወያይቶ ስምምነት ላይ ደርሷል። ለሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት ድርጅቱን የሚመሩ የ አመራር አባላትን መርጧል። በሀገር ውስጥና በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የኢሕአፓ ወክንድ ዓላማዎች ስለሚስፋፉበት፤ ትግሉም ስለሚጠናክርበት ሁኔታ ጉባዔው በሰፊው ተወያይቶ እቅድና መመሪያ ለአመራሩ ሰጥቷል።

በሀገራችን በተካሄደው የዴሞክራሲ ትግል ከፍተኛ መስዋእትነትን ከፍሎ ትግሉ እንዲቀጥል ያደረገው የኢሕአፓ ልጅ የ ኢሕአወሊን የትግል ገድል ምግብ በማድረግ ከዛሬ 35 [ዓመት በፊት የተጀመረውን ሕዝባዊ ትግል በማጠናከርና በማጦዝ ኢትዮጵያን ከጥፋት ለመታደግ የኢሕአፓ የወጣት ክንፍ ሆኖ የተቋቋመው ኢወክንድ ጠላትን መጣንብህ በማለት ቁርጠኛነቱን ሲገልጽ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ ከጎናችሁ ነን፣ መጥተንላችኋል የሚል መልእክት ያስተላልፋል። የኅብረተሰቡ ትኩስ ኃይል የሆኑት ወጣቶችም፤ የድርጅታንን ሕዝባዊ ዓላማ ተረድተው ተቀላቅለውን ትግሉን አብረን እንድናጠናክር ጥሪ እናስተላልፋለን።

ባለፉት 40 ዓመታት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ምትክ አልባ የሆነውን ህይወታቸውን የሰጡ የታላላቅ ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን ፈለግ ተከትለንና አርማቸውን ከፍ አድርገን፤ የተከፈተባቸውን የታሪክ ብረዛ ተቋቁመን ትግሉን አጠናክረንና አምባገነን አገዛዝን አስወግደን ለመጭው ትውልድ በክብር ለማስተላለፈ ቃል እየገባን ነው።

ሕዝቡ በትግሉ ድሉን ይቀዳጃል

የኢሕ አፓ የወጣት ክንፍ ድርጅት
ሰኔ 22 ቀን 2001
ቺካጎ

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: join@eprpy.com
www.eprpy.com